አፍሪካ ቲቪ

4

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት

# የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

በቴሌግራም

4

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

- ሱረቱ አል-ኢኽላስ
- (የፍፁምነት ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የምእራፉ ብዛት (4) ናቸው፡፡
- ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-
- አላህ በንግሥናውና በአምላክነቱ ምሉዕ መሆኑን እና
- ከጉድለት የጠራ (የላቀ) መሆኑን የሚያረጋግጥ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ይህ ምዕራፉ የወረደበትን ምክንያት በተመለከተ ሁለት ዘገባ የተዘገበ ሲሆን፡- የተወሰኑ ሙሽሪኮች ወደ ነብዩ صلى الله عليه وسلم መጥተው ሙሐመድ ሆይ! አላህ መልአክን ከብርሃን፤ አደምን ከጭቃ፤ ኢብሊስን ከእሳት፤ ሰማይን ከጭስ፤ እና ምድርን ከውሃ አረፋት ፈጠረ፡፡ እስቲ ጌታህን ከምን እንደተፈጠረ ግለፅልን? ከምንድን ነው የተሰራው? ከወርቅ ወይስ ከብር ወይስ ከነሀስ? ይበላል ወይስ ይጠጣል? ብለው በመጠየቃቸው ነው የወረደው፡፡ (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ፤ አህመድና ቲርሚዚ) ይህ አንቀፅ ሶስቱንም የተሳሳቱ ቡድኖች ማለትም፡- ሀ. መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው የሚሉትን የዐረብ አጋሪዎች፤ ለ. ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው የሚሉት አይሁድና ሐ. መሲሕ የአላህ ልጅ ነው የሚሉትን ክርስቲያኖችን በአንድ በቂና የማያዳግም መልስ ይሰጣል፡፡

4

- በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)
- (1) (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)፡- <<አላህ በአምልኮ ብቸኛና አንድ ነው ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም>> እርሱ አላህ አንድ ብቻ ነው፡፡ በላቸው።
- (2) አላህ በሙሉእነትና በውበት መገለጫዎቹ ረገድ የበላይነቱ ከሁሉ የላቀ ታላቅ ነው። ፍጡራን በሙሉ ወደ እርሱ ተጠጊዎችና ከእርሱ ፈላጊዎች ናቸው። አላህ የሁሉ ነገር መጠጊያ ነው፡፡
- (3) አልወለደም፤ አልተወለደምም፡፡ ማንንም አልወለደም፤ ከማንም አልተወለደም። ልጅም ሆነ ወላጅ የለውም (የተቀደሰ ጌታ ነው)።
- (4) ለእርሱ አንድም ቢጤም አምሳያም የለውም በል፡፡

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ፋሓ")

አፍሪካ አካዳሚ

## ከፍፁምነት ምዕራፍ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. አላህ የምንለዉን ሁሉ የሚሰማንና የምንሰራዉን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን፤
- 2. የአላህን አንድነት ና ብቻውን ሊመለክ የሚገባው ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤
- 3. ለፈጣሪ ልጅ፤ ሚስት፤ እሱን መሰል ቢጤ አለው ማለት መሰረተ ቢስ አባባል መሆኑን፤
- 4. አላህ ልጅ፤ ሚስት አለው ማለት ኩፍር (ክህደት) መሆኑን፤
- 5. የነብዩ መሐመድን صلى الله عليه وسلم ነብይነትን ማረጋገጥ፤
- 6. አንድም ስልጣኑን መጋፋት የሚችል፤ ሌላ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤
- 7. አላህን በስሞቹና በባህሪያቱ ማወቅ ተገቢ መሆኑን እንማራለን፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio